ከብርሃን አሰፋ
23-02-2020

የዛሬ መጣጥፍ ርዕስ ማህበራዊ ምህንድስና/ Social Engineering የሚል ሲሆን እርዕሱን የመረጥኩበት ምክንያት ደግሞ አገራችን ያለችበትን ወቅታዊ ሁኔታ በተገቢውየሚገልፅና መፍትሄ የሚሆንም ሃሳብም ስላለው ነው::

ማህበራዊ ምህንድስና/Social Engineering

ማህበራዊ ምህንድስና ልክ አንድ ስቪል ኢንጂነር በትምህርት: በቴክኖሌጂ: በእቅድ እና በእውቀት ተመርቶ ለስው ልጇ ዘመኑን የዋጀ የመኖሪያ ቤት: የመንገድ አገልግሎት እንዲሁም የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪዎችን ሰርቶ ለህብረተስቡ መገልገያ እንደሚያቀርበው ሁሉ የማህበራዊ ምህንድስና ዋና አላማ ዘመኑን የሚመጥኑ ህብረተስብን እንደ ሊም በማያያዝ ጤነኛና ሠላማዊ ህብረተስብ መፍጠር እንደሚቻል የሚያስተምር አስተምህሮ ነው::

ማህበራዊ ምህንድስና የሚለውን ስርዎ ቃል ለመጀመሪያ ግዜ የተጠቀመው ፈላስፋ ስም Karl Popper የሚባል ሲሆን ቃሉን በሰፊው ለንባብ ያበቃውና ያስተዋወቀው ደግሞ እውቁ ሶሲዎሎጂስት Zygmunt Baumann ነው:: Zygmunt “Modarnity and the Holocaust” በሚለው መፅሃፉ የጀርመን ናዚ እንዴት እድርጎ የይውህዳ ዘሮችን በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ግዜ እንደጨረሳቸው የሚተነትን መፅሃፍ ነው::
መፅሃፉ በመቀጠልም ናዚ ያደረግውን ጭፍጨፋ ያወግዛል:: Zygmunt ከላይ በተጠቀስው መፅሃፍ ላይ የማህበራዊ ምህንድስና እስተሳሰብ ውስጥ ሁለት ዓይነት ተቃርኖዎች እንዳሉ ያስረዳል::

የመጅመሪያው የማህበራዊ ምህንድስና አስተሳስብ አንድ ሃገረ መንግስት እንዴት አድርጎ የበለፀገ: በውስጡ ስምምነትየነገሰበት: ጤነኛና በእድገት ጉዳና የሚገስግስ ህብረተስብን መፍጠር ይቻላል የሚል ሲሆን ይህን ሃሳብ ከግብ ለማድረስ ደግሞ ዘመኑ ያመጣቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶችን እና የሰለጠነና የተማረ የሰው ሃይል በማሰማራት harmonious and balanced society መፍጠር እንደሚቻል የሚያስተምር ቲዬሪ ነው:: ይህን ቲዬሪ ምንአልባት አንዳንዶቻችን ሊደረስ የማይችል መናባዊ(utopia) ሊመስላችሁ ይችላል ግን እኔ በምኖርባት ዴንማርክ ውስጥ ይህ እውን ሆኖ እያየሁት ሰለሆነ የሚቻል ነገር መሆኑን በእርግጠኝነት አበስርላችሁ አለሁ:: ይህ ከላይ የጠቀስኩት የማህበራዊ ምህንድስና አስተሳሰብ ፈረንጆች the manifest form of social engineering ይሉታል:: ልክ ያገሬ ስው የአንድን ነገር ሁለተኛ ገፅታን ሲገልጥ " የአንድ ሳንቲም ሁለተኛው ገፀታ" እንደሚለው ማለት ነው ወደ ሁለተኛውና latens form of social engineering ወደሚሉት የማህበራዊ ምህንድስና መጥፎ ገፅታ ስናይ ደግሞ የ 20ኛውን ምዕተ ዓመትን ጀርመንን እንደምሳሌ እንጠቅሳታለን::

Adolf Hitler በጀርመን ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ከአርያን ዘር ውጭ የነበሩት በተለይ ደግሞ የጂው ዘር አለባቸው ያላቸውን ወደ 6mio. የሚጠጉ ስዎችን ዘመኑ ባመጣው ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተጠቅሞ ዶግ ዓመድ አደረጋቸው:: እንግዲህ እዚህ ላይ መገንዘብ የምንችለው Hitler እንዴት አድርጎ የማህበራዊ ምህንድስናን አስተሳስብ ይውልበታል ከተባለው ዓላማ ውጭ በመጠቀም የሁለተኛውን የዓለም ጦርንት እንዳስነሳና ለብዙ ሚሊዮን ህዝብ ጥፋት መንስዔ እንደሆነ ያሳየናል ማለት ነው::

በወቅቱ አስተሳስቡን የፈጠሩት ፈላስፎች ምክንያት ከላይእንዳልኩት በበጎመልኩ ተጠቅመን ህብረተስብን ወደ ተሻለ የእድገት ጎዳና የሚወስድ ትልም ነበር ምክንያታቸው ነገር ግን ግንዛቤው መጥፎ ስዎች እጂ ገብቶ ጉድ አፈላ እንጂ::

Hitler መፍጠር የፈለገው እንድ ዓይነት ዘር ያውም የዓርያን ዘር በምድረ ጀርመን ብሎም በአውሮፓ መፍጠር ነበር:: homogeneous የሆነ ማህበረ ስብ ለመፍጠር ደግሞ ከዓርያን ዘር ውጭ ያሉት በጋዝ ቻምበር መርዞ መግደል ነበረበት::

ይህን ማህበራዊ ምህንድስና የሚለውንአስተሳስብ ዛሬ ሳቀርብ ያለ ምክንያት አይደለም:: ይህ ከላይ የገለፅኩት Hitler latens በሆነ መልኩ የተገበረው የማህበራዊ ምህንድስና አስተሳስብ ወደ አገሬ ኢትዮጳያ ከገባ ወደ 30 ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም አሁን አሁን እያየነው ያለነው ሁኔታ ልክ Hitler እንደአደረገው የሚመስል ነገር እየተከስተ በመሆኑ ይህን ዕርእስ ማንሳቱ ተገቢና ወቅታዊ ሆኖ ሰለአገኘሁት ነው::

አገራችን ለገባችበት ፓለቲካዊ : ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ተጠያቂው ወያኔ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለኝም:: ምክንያቱም አገሪቱን በባንቱስታን አስተሳስብ ቀምሮ በ9 ክልሎችና በ2 ልዩ አስተዳደሮች ከልሎ ይህን የzenawisme አስተሳስብ በህገ መንግስት አስደግፎ እርስ በእርሳችን እንድንናቆር አድርጎል::

ወያኔ በህዝብ እቢተኝነት ተገፍቶ ከመናገሻ ከተማዋ አዲስ አበባ ለቆ መቐለ ከከተመ በኋላ የመጣው የአዴፓ መራሹ መንግስት ደግሞ በተረኝነት መንፈስ መጥቶ ወያኔ የሄደበትን መንገድ በመቀጠል የአገራችንን እጣ ፈንታ አደጋ ላይ እንዲወድቅ ምክንያት ሆኖል:: በውያኔ መራሹና በአዴፓ መራሹ መሃል ምንም ዓይነት የእርዕዮት ዓለምም ሆነ የፓለቲካ ልዮነት የለም:: ልዩነቱ የስልጣን ብቻ ነው:: እንደዛ መሆኑን የሚያረጋግጠው ደግሞ ምንም አይነት ይህግም ሆነ ያወቃቀር ልዩነት አለመኖሩ ነው::

የአዴፓ መራሹ ቡድንን ከወያኔ የሚለየው ወያኔ የአገሪቱንም ሆነ የክልሎችን ሰልጣን በሃይ ይዞ የማንቀጥቀጥ ባህሪ ነበረው:: ያው ሁሉንም የኢህአዴግ አባል ድርጅቶችን የፈጠራቸው እሱ በመሆኑ:: የአዴፓ መራሹ መንግስት ግን ከመናገሻ ከተማዋ ውጭ ምንም አይነት አቅም የሌለው ሲሆን: በሱ ስርወ መንግስት የመንጋ እንቅስቃሴ ገኖ የተደራጁ ወጣቶች የፈለጉትን የሚያደርጉበት ግዜ ሆኗል:: መንግስት ትልቁንን እና ዋናውን የመኖሩ ምክንያት የሆነውን ህግን የማስከበር እና ዜጎች በሰላም ገብቶ መውጣትና መስራት እንዲችሉ ማድረግ ሲሆን ይህን ምግባሩን በመንደር ወመኔዎች ተነጥቆ ወይንም የመንደር ወመኔቹ ይሚፈፅሙትን ወንጀል የህግ ጠለላ በመስጠት ለብዙ ዜጎች ሞትና መፈናቀል ምክንያት ሆኗል::

አሁን የኦሮሚያ ክልል ተብሎ በሚጠራው የኢትዩጵያ ግዛት ውስጥ ልክ Hitler Gestapo ብሎ ወጣቱን እንዳደራጀው የኦሮሞ ፅንፈኞች ደግሞ ቄሮ የሚል መንጋ አደራጁተው በኦሮሚያ ክልል የሚኖሩ ኢትዩጵያውያን በመግደልና በመዝረፍ ልክ Hitler በጂዎች ላይ እንዳደረጉት ቄሮም ወደዛ የሚወስደውን መንገድ ተያይዞታል:: በኦርቶዶክስ እምነት ላይ እየተደረገ ያለው ወከባም ኢትዩጵያን ከማፍረስ ሂደት ጋር የተያያዘ ነው:: ከሌላው ኢትዩጵያዊያን ነፅ የሆነችና ወጥ/Homogin ኦሮሚያን መፍጠር የሚለው latens የሆነው የማህበራዊ ምህንድስና አስተሳሰብ ለመተግበር ደፋ ቀና እያሉ እንደሆነ በገሃድ እያየን ነው::

ታዲያ ይህ አይነት አካሄድ ለማንኛችንም ጠቃሚ ያልሆነና አገሪቱንም ወደ ገደል እወሰደ በመሆኑ:
ዘርን ያማከለ የፓለቲካ አካሄድ የእብደት መንገድ ሰለሆነ:
ፅንፈኝነት ለመፍትሄ በጣም የራቀ በመሆኑ ሊቀየር ይገባል እላለሁ::

ታዲያ ጥያቄው እንዴት እንቀይረው የሚለውን መመለስ ተገቢ ነው እላለሁ::

እኔ መፍትሄ ብየ የማቀርበው ከዚህ በታች እንደሚከተለው ይሆናል::

እውነት ነው ኢትዩጵያ አገራችን የብዙ ቋንቋዎች : ባህሎች እንዲሁም ማንነቶች ስብስብ ውጤት ነች:: ይህን አይነት መስተጋብር ፈረንጆቹ Cultural Relativisme ይሉታል:: Cultural Relativisme ወይንም ህብረ ብሄራዊነት ትኩረት የሚያደርገው ሁሉም ባህሉች በእኩል እንዲስተናገድ እያንዳንድ ባህል ደግሞ የራሱየሆነ መገለጫ እና ውስጣዊ አመክንዩ/ logic ያለውመሆኑን ነው የማህበራዊ ሳይንስ ባለሞያወች የሚናገሩት::

ይህ Cultural Relativisme የተባለው አስተሳስብ በአንድ በኩል Evolutionistic ማለትም ያንድን ethinicity dominance የሚቃወም ሲሆን  በሌላበኩል ደግሞ Essentialistic/ በአንድአገር ውስጥ ያሉ የተለያዩ  ባህሎች ወሰናቸው የተከለለ/demarcated የሆነ: ዝግ ምንም አይነት የማህበራዊ መስተጋብር ከሌሎች ጋር እንዳያደርጉ የሚገድብ: በራሳቸው ወግና ማህበራዊ ግንኙነት ተወስነው በራሳቸው ዛቢያ ብቻ የሚሺከረከሩ እንዲሆኑ የሚያደርግና paradoxal የሆነ አመለካከትንም ያራምዳል:: cultural Relativism የሚለው አስተሳብ እንደ እስተሳስብ ጥሩቢመስልም በተግባር ግን ተፈትኖ መውደቁን ኢትዩጵያ አገራችን ምስክር ናት::

ኦቦ በቀለ ገርባ እንደተናገረው ደግሞ "በኦሮሚያ ክልል ከሚኖሩ አማሮች ጋር የጋብቻም ሆነ የንግድ ልውውጥ ለማድረግ አማራው ወደ ኦሮሞው የንግድ ቦታ ሲሄድ የንግድ ልውውጡ በኦሮምኛ ካልሆነ ኦሮሞው ዕቃውን እንዳይሸጥለት ይመክራል" ኦቦ በቀለ ገርባ ይህን ሲል የኦሮሞው ባህል ዝግ እንደሆነ: ማህበራዊ ትስስሩም ከኦሮሞው ብቻ እንድሆነና ባህል ከሰወች ጋር በምታደርገው እለታዊ መስተጋብር እንደሚቀየርና እንደሚያድግ የካደ essentialistic aspect እንዳለው አሳይቶናል:: ይህ ማለት ደግሞ ስዎች ባህልን በሚኖራቸው ማህበራዊ ግንኙነት እንዳያሳድጉት ባህል በተወሰነ ethicity ብቻ ታጥሮ እንዲቀርና ዲያለክቲካዊ መስተጋብሩን የሚገድብ ነው የሚሆነው:: ይህ አመለካከት ታዲያ ወደ መቀራረብና ወደ መፍትሄ አያመጣንም:: ምክንያቱም ethinocentrismን እንድ ፍልስፍና ይዘን ብሄራዊ መፍትሄ የሚባል ነገር እማይታስብ ሰለሆነ::

እንግዲህ ከላይ የአንድ ዘር የበላይነት ( Evolutionistic) ሌሎችን ባህሎችና ማንነቶች የሚጨቁን ሰለሆነ ልንከተለው እንደማይገባ አስቀምጫለሁ:: እንዲሁም Cultural Relativism እኛ እና እናንተ የሚል dicotemy ሰለአለውወደ ፍጂት ሊወስደን መሆኑንም ሁላችን እያየነው ያለ ሃቅ ነው:: ሰለዚህ ይንንም ሃሳብ በፅኑአውግዘን የተሻለ መፈለግ ይኖርብናል::

እኔ መፍትሄ ነው ብየ የማስበው አስተሳስብ Contextuel Cultural perception በግርድፉ ሰተረጉመው ደግሞ ዐውደ ባህላዊ ግንዛቤ የሚል ይሆናል:: ይህ ግንዛቤ ለአገራችን መልከ ብዙ ችግሮች መፍትሄ ይሆናል ብየ አስባለሁ:: ምክንያቱም አስተሳሰቡ የተፈጥሮን ህግን የተከተለ በመሆኑ ነው::

የዐውደ ባህላዊ አስተሳስብ የሚያጠነጥነው "ሰው" ሰው በመሆኑ ብቻ አሰበው እና ግንኙነታችንም "ዘርን" ያማከለ ከሚሆን "ሰውን" ያማከለ ይሁን ምክንያቱም ሰው ተፈጥሮዊ ሲሆን "ethinicity” ደግሞ ሰው ሰራሺ በመሆኑ:: የሰውን ልጂ ሰነልቦና ቤተሰብና ማህበረሰብ ነው የሚቃኙት:: ታዲያ ከአካባቢው በሚያገኘው አዋንታዊም ሆነ አሉታዊ ተፅዕኖዎች የሰው ልጂ ይቃኛል:: ታዲያ የእኛ ግንኙነት መሆን የሚገባው ሰውየው ባዳበረው ልምድና ተሞክሮ ሚዛን ውስጥ በማስገባት አስተሳሰቡ ከእኔ ጋር ይሄዳል ወይንስ አይሄድም? ካልሄደስ እንዴት ነው ልዩነታችንን ማጥበብ የምንችለው የሚለው አስተሳሰብ ሰውኛ ነው ባይ ነኝ:: የእኔን አይነት ቋንቋ ተናጋሪ ነው: ባህሉ ይእኔን ይመስላል ብለን ስንሄድ አደገኛና ግዜውንም የማይመጥን አስተሳሰብ ሰለሆነ ወደ ሰውነታችን እንመለስ እላለሁ::

ባህል ደግሞ በሰዎች ዕለታዊ ግንኙነቶች የሚፈጠር: የሚያድግ : የሚሞትና ባዲስ መልክም የሚፈጠር የግንኙነት ውጤት እንጂ ባለበት ቆሞ የሚቀር አይደለም:: በcultural Relativism አስተሳሰብ ግን ባህል የማያድግና የማይለወጥ የአንድ ዘር መገለጫ ብቻ እንደሆነ ነው ታሳቢ የሚያደርግ ነው::

ፁሁፌን ሳጠቃልል ወደ መፍትሄው ሊያመጣን የሚችለውን ይዘን አገራችንን ወደ ሠላማዊ ጎዳና የሚወስዳትን ዐውደ ባህላዊ አስተሳሰብን ብናዳብር ችግራችንን ሊፈታልን ይችላል ባይ ነኝ::

አሁን አገራችን እየተከተለችው ያለው አስተሳሰብ የጥላቻ: የጥፋት: የዘረኝነት ሰለሆነ በህግ ሊታገድ ይገባል እላለሁ::

ከብርሃን አሰፋ ዘ ሓገረ ዴንማርክ::